## የጅማ ዩኒቨርሲቲ የ2010 ዓም የፌዴራል ኦዲት ግኝት አጭር መግለጫ

| ግኝት | በመጀመሪያው ሪፖርት(ማኔጅመንት ሌተር) ላይ የቀረበ ግኝት | | | በመጨረሻው የኦዲት ሪፖርት ላይ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | በቀረበ ማስረጃና በተሰጠ ማብራሪያ ከግኝት የወጣ | በመጨረሻው ኦዲት ሪፖርት ላይ የወጣ | የቀረበ ግኝት ብዛት | ሙሉ በሙሉ ግኝቱ እንዲወጣ የተጠየቀ | የእርምት እርምጃ መርሃ ግብር የተዘጋጀለትና እርምጃ እየተወሰደበት ያለ |
| የ2010 ግኝት | 30 | 18 | 12 | 12 | 6 | 6 |
| የክትትል ኦዲት (የ2009 እና ወደኋላ) | 10 | 4 | 6 | 6 | 2 | 4 |
| ድምር | 40 | 22 | 18 | 18 | 8 | 10 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በ2010 ዓም የፌዴራል ኦዲት የመጀመሪያ የማኔጅመንት ሌተር በግኝትነት ከቀረቡት 40 ግኝቶች ውስጥ 30ዎቹ ማስረጃና ማብራሪያ በማቅረብ እንዲወጡ የተደረጉ/የተጠየቁ ሲሆኑ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ መርሃግብር ተዘጋጅቶባቸው የትግበራ እንቅስቃሴ እየተካሄደባቸው ያሉ አስር ግኝቶች ናቸው፡፡

## በ2010 ዓም የፌዴራል ኦዲት የመጨረሻው ሪፖርት ላይ ስለቀረቡ ግኝቶች ዝርዝር ማብራሪያ

| የጉዳዩ መለያ | የጉዳዩ መለያ ውጤት | ምርመራ |
|---|---|---|
| **ግኝት1፡- የውስጥ ገቢና ፕሮጀክት ሂሳብ አመዘጋገብ** | የዩኒቨርሲቲው ህክምና ማዕከል የ2010 ዓም የውስጥ ገቢ የተሟላ ምዝገባ የሌለውና ሪፖርት የሌለው መሆኑ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስዔ** | ሪፖርቱ በየጊዜው ተሰርቶ የነበረ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው ደረጃ የ IBEX ሶፍትዌሩ በመሃል ሲቋረጥ ሙሉ መረጃው ስለጠፋ እና በከፍተኛ የፋይናንስ ባለሙያዎች እጥረት | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበው ገንዘብ ከወጪ ቀሪ በበጀት አመቱ መጨረሻ ሪፖርት አለማድረጉ የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ ገቢ የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛነት ላያሳይ ይችላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | በተደረገው ጥረት አሁን እስከ ሰኔ 2010 ዓም ያለው ሪፖርት ተሰርቶ ተጠናቋል | ከግኝት እንዲወጣ በመርሃ ግብሩ ዶኩመንት ላይ ተጠይቋል |
| **ግኝት2- ደመወዝና ተዛማጅ ክፍያዎች** | ከህንድ ሀገር መምህራን ደመወዝ ላይ የሥራ ግብር ያልተቀነሰ ስለመሆኑ፤ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስዔ** | ቀደም ሲል ግልፅ የሆነ መመሪያ ባለመኖሩ | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ከስራ ግብር ላይ መንግስት የሚያገኘውን ገቢ ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ያሳጣዋል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ዩኒቨርሲቲው ግልፅ መመሪያ ከገንዘብ ሚ/ር ከደረሰው ጀምሮ ግብሩን እየቀነሰ ነው | ከግኝት እንዲወጣ በመርሃ ግብሩ ዶኩመንት ላይ ተጠይቋል |
| **ግኝት3-ደመወዝና ተዛማጅ ክፍያዎች** | ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ለሚላኩ መንግስት ሠራተኞዎች በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው ብቻ እንደሚከፈል ቢደነግግም በአንድ ኮሌጅ አንድ መምህር ከደመወዝ መጠን ብር 8,310.00 ግማሽ ደመወዝ መከፈል ሲገባ ሙሉ ደመወዝ በመከፈሉ በብልጫ ብር 12,465.00 የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስዔ** | በኢንስቲትዩቱ የተጠቃለለ ፔይሮል ይሰራ የነበረው ወደ ሶስት ፋኩልቲ ሲከፈል የተፈጠረ ስህተት | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ከመመሪያ ውጪ ሙሉ ደሞወዝ ክፍያ የመንግስትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡ ከመንግስት መመሪያ ውጪ የሚፈጸም ክፍያ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ግኝቱ ከታወቀ ቦሃላ ከየካቲት ወር 2011 ዓም ጀምሮ የደመወዛቸው 1/3 እየተቆረጠ ገቢ እየተደረገ ነው፡፡ | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |
| **ግኝት4- ደመወዝና ተዛማጅ ክፍያዎች** | ለመምህራን በመንግስት የተሻሻለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተፈቀደው አግባብ የክፍያ ተመን ሳይኖረው ከህግና መመሪያ ውጭ ከመደበኛ በጀት ለውስጥ ፈታኞች እና ለውጭ ፈታኞች ክፍያ በሚል በየኮሌጆች በድምሩ 1,137,177.00 ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስዔ** | በሃገሪቱ ወጥ የሆነ መመሪያ ባለመኖሩ የተፈጠረ ክፍተት | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | በመንግስት ወይም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ የክፍያ ተመን ሳይኖር ክፍያ መፈጸም ለገንዘብ ብክነት መከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ተጠያቂነት ያመጣል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ቀደም ሲልም በሃገሪቱ ወጥ የሆነ መመሪያ ባለመኖሩ አቻ የተቋማትን ልምድ በመቅሰም ዝቅተኛ ክፍያ ነበር የሚከፈለው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በተደጋጋሚ ት/ት ሚ/ር መመሪያ እንዲያወጣ ሲጠይቅ የነበረ በመሆኑ በዚህ | ቀደም ሲል ለተከፈሉ ክፍያዎች ክፍተቱ ከዩኒቨርሲቲው የተፈጠረ ባለመሆኑና |

| | | |
|---|---|---|
| | ዓመት መመሪያው ፀድቆ ወጥቷል፡፡ | ዩኒቨርሲቲውም ከፍተኛ ጥረት ያደረገ በመሆኑ ከግኝት እንዲወጣ በመርሃ ግብሩ ዶኩመንት ላይ ተጠይቋል |

**በ2010 ዓም የፌዴራል ኦዲት የመጨረሻው ሪፖርት ላይ ስለቀረቡ ግኝቶች ዝርዝር ማብራሪያ**

**..... የቀጠለ**

| የጉዳዩ መለያ | የጉዳዩ መለያ ውጤት | ምርመራ |
|---|---|---|
| **ግኝት5- የእቃዎችና የአገልግሎቶች ግዢ /ያልተቀነሰ ዊዝሆልዲንግ ታክስ በተመለከተ/** | የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 48,327.81 ለሚገዛቸው ግዥዎች ግብርን ቀንሶ ክፍያ ያልፈጸመ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስኤ** | በከፍተኛ የሰው ሃይል እጥረት እና የክትትል ማነስ | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | - ከክፍያ ላይ የሚሰበሰብ ቅድመ ታክስ(withholding) ገቢ በማግኘት አነስተኛውን ምጣኔ የታክስ ግዴታቸውን ሳይወጡ ሊሰወሩ ይችላሉ፡፡<br>- መመሪያን ያልተከተለ አሰራር ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡<br>- መንግስት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣው ከመቻሉም በላይ ለመንግስት ገቢ መሆን የሚገባው ገንዘብ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | የአንዱ አቅራቢ በወቅቱ ግብሩ ተቀንሷል፡፡ የሌሎቹ ግኝቱ እንደተገኘ ከአቅራቢው ጋር በመነጋገር ግብሩ እንዲቀነስ ተደርጓል፡፡ | ከግኝት እንዲወጣ በመርሃ ግብሩ ዶኩመንት ላይ ተጠይቋል |
| **ግኝት6- የእቃዎችና የአገልግሎቶች ግዢ /ያለማስረጃ በብልጫ የተከፈለ/** | በህክምና ማዕከሉ ብር 19,539.78 ያለማስረጃ ለአቅራቢ በወጪነት ተመዝግቦ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስኤ** | በከፍተኛ የሰው ሃይል እጥረት እና የክትትል ማነስ | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ዩኒቨርሲቲው ያለ በቂ ማስረጃ የሚከፈል ሂሳብ የሚያወራረድና ክፍያ የሚፈፅም ከሆነ ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን እንዳይታወቅ እና ውስን የመንግስት ሀብትን ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ግኝቱ እንደታወቀ ለአቅራቢው ተነግሮት ገንዘቡን እንዲመልስ ተደርጓል | ከግኝት እንዲወጣ በመርሃ ግብሩ ዶኩመንት ላይ ተጠይቋል |
| **ግኝት7- የእቃዎችና የአገልግሎቶች ግዢ /የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበበት/** | የጅማ ዩኒቨርሲቲ ፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለምግብ ግብዓቶች ግዥ ወጪ ላደረጋቸው ክፍያዎች ብር 2,778,747.78 ክፍያ ሲፈጽም ገንዘቡን ስለመቀበላቸው የሚያሳይ የገቢ ደረሰኝ አለመኖሩ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስኤ** | በከፍተኛ የሰው ሃይ እጥረትና የክትትል ማነስ | |

| | | |
|---|---|---|
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊዉ የወጪ ማስረጃ ሳይሟላ ክፍያ የሚፈጽም ከሆነ ስለ ክፍያዉ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ ያለ መያዝና በኦዲት ወቅት በአግባቡ ያለማቅረብ ችግር እንጂ ክፍያው ሲፈፀም በወቅቱ ደረሰኙ የቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃው ተያይዟል፡፡ | ከግኝት እንዲወጣ በመርሃ ግብሩ ዶኩመንት ላይ ተጠይቋል |

**በ2010 ዓም የፌዴራል ኦዲት የመጨረሻው ሪፖርት ላይ ስለቀረቡ ግኝቶች ዝርዝር ማብራሪያ**

**..... የቀጠለ**

| የጉዳዩ መለያ | የጉዳዩ መለያ ውጤት | ምርመራ |
|---|---|---|
| **ግኝት8- ቋሚ ንብረቶችና ግንባታ /የዘገየ ግንባታ/** | ዩኒቨርሲቲው ለሚያስገነባው የላብራቶሪና ወርክሾፕ ግንባታ ስራዎቹ 488 ቀናት ዘግይተው የተጠናቀቁ ቢሆንም ለዘገበት ቀናት ምክንታዊ ላልሆኑ መዘግየቶችና ምክንያታዊ የሆኑ መዘግየቶች ከተገለፁ በሁዋላ ምክንያታዊ ላልሆኑት የጉዳት ካሳ ተሰልቶ እንዲከፈል ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስዔ** | የግንባታዎች መጓተት | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ሥራ ተቋራጩ ምክንያታዊ ላልሆኑ መዘግየቶች በዩኒቨርሲቲው ላይ ጉዳት በአማካሪ መሃንዲሱ መሰረት ተሰልቶ የማይከፈል ከሆነ ለደረሰው ጉዳት ለዩኒቨርሲቲው መከፈል ያለበት ገንዘብ እንዳይከፈል ሊያደርግ ይችላል፡፡ ግንባታዎች መዘግየት መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ድርጅቱ ያልተከፈለው ሂሳብ ስላለ አማካሪው ስሌቱን በአግባቡ ሰርቶ እንዲያመጣ የታዘዘ በመሆኑ በሚፀድቀው የክፍያ ሰነድ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |
| **ግኝት9- የእቃዎችና የአገልግሎቶች ግዢ /ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ/** | የጤና ኢንስቲትዩት ብር 254,362.17 ለከሃሊ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ/ማህ ክፍያ ሲፈጸም ጠቅላላ ለዘገየበት 38 ቀናት ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ ብር 9,665.76 የተገኘ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል። | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስዔ** | የክትትል ማነስ | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | አቅራቢዎች በውለታው መሰረት ባለመፈጸማቸው መከፈል ያለበት የጉዳት ካሳ ሳይቀነስ ክፍያ መፈጸም መንግስት /ተቋሙ/ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ያሳጣል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ግኝቱ ከታወቀ ቦሃላ ለአቅራቢው ደብዳቤ ተፅፏል፡፡ አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |
| **ግኝት10- ተሰብሳቢ ሂሳብ / በወቅቱ ያልተወራረደ/** | በድምሩ ብር 573,654.20 ያልተወራረደ ሂሳብ፤ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስዔ** | ቀደም ካሉ ረዥም አመታት በፊት የተጠናከረ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ባለመኖሩ ሂሳቡ ሲንከባለል የመጣና እና የቅርቡ ደግሞ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የምርምር ድጋፍና የመምህራን የምርምር ድጋፍ ሂሳብ ግለሰቦቹ በአካባቢው ባለመኖራቸው ሳይወራረድ መቆየቱ | |

| | | |
|---|---|---|
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ሳይወራረዱ ለረጅም ጊዜ ማቆየት የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ዓመታዊ ሂሳቡን በወቅቱ ዘግቶ ሪፖርት እንዳያቀርብ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | በ2010 የኦዲት ግኝት የእርምት እርምጃ መርሃ ግብር ላይ እንደተገለፀው በግኝቱ ከተገለፀው ውስጥ ብር 146,205.66 ተወራርዷል፡፡<br><br>ቀሪዎቹ በህግ አገልግሎት የተያዙ፣ በፍርድ ቤት ተወስነው ለገ/ሚ/ር ቀርበው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ቀሪዎቹ በዩኒቨርሲቲው ክትትል ተደርጎባቸው የሚወራረዱ ይሆናል፡፡ | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |

**በ2010 ዓም የፌዴራል ኦዲት የመጨረሻው ሪፖርት ላይ ስለቀረቡ ግኝቶች ዝርዝር ማብራሪያ**

**..... የቀጠለ**

| የጉዳዩ መለያ | የጉዳዩ መለያ ውጤት | ምርመራ |
|---|---|---|
| **ግኝት11- ተከፋይ ሂሳብ /በወቅቱ ያልተወራረደ/** | ሰኔ 30/2010 በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በድምሩ ብር 13,472.53 ያልተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል | |
| **መስፈርት** | **ደንብና መመሪያ** | |
| **መንስኤ** | ተከፋዩን ለይቶ አለማወቅ/ተከፋዩ ቀርቦ አለመውሰድ | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ተከፋይ ዕዳዎች በወቅቱ ካልተከፈሉ በቆይታ ብዛት ከፍተኛ የዕዳ ክምችት እንዲፈጠር ሊዳርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ዓመታዊ ሂሳቡን በወቅቱ ዘግቶ ሪፖርት እንዳያቀርብ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ብር 7,398.01 ለተከፋዮቹ ተከፍሎ ሂሳቡ ተወራርዷል፡፡ ቀሪው በሁለት ኮሌጆች የሚታየው ተገቢው እርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |
| **ግኝት12- የቋሚና አላቂ ንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አስተዳደር** | የሚወገዱ የተለያዩ ዕቃዎች (ኮምፒዩተሮችና አክሰሰሪዎች፣ ወንበር ሸልፎች፣አልጋዎች፣...ወዘተ) የተለያዩ እርምጃዎች ሳይወሰዱ ተከማችተዉ መገኘታቸዉ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስኤ** | ንብረቶቹን እንዲረከብ የተፈቀደለት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እቃዎቹን በወቅቱ ባለማንሳቱ እና ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አፋጣኝ መፍትሄ አለመሰጠቱ | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | በከፍተኛ የመንግሥት ገንዘብ ወጪ ሆኖ የተገዙ  ንብረቶች መመሪያዉን መሰረት በማድረግ ካልተጠበቁ ንብረቶቹ ለብልሽት ሊዳረጉና በወቅቱ ሥራ ላይ ካልዋለ አላግባብ ሊጠፋና ሊበላሽ ይችላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ዩኒቨርሲቲው በንብረት ማስወገድ ጥረቱ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ተገቢ እውቅና አለው፡፡ በአሁኑ ሰዓትም በመርሃ ግብራችን መሰረት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የተለያዩ ንብረቶች በመወገድ ላይ ናቸው | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |
| **ግኝት 13.1 እና 13.2 - የህጋዊነት/የክትትል ኦዲት /2003-2009/** | በመንገድ ግንባታ ሥራ ምክንያት ለፈረሱ ለካሳ ክፍያ ተብሎ ተማሪዎች መዝናኛ ክበብ ብር 4,517,544.47 እንዲሁም ለኮሚዩኒቲ ት/ቤት  ብር 8,812,578.98  በድምሩ 13,330,123.45 ከተቋሙ ሂሳብ ወጪ በማድረግ የተከፈለው ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስኤ** | ቀደም ሲል በነበረው የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ግልፅነት ብዥታ እና ዩኒቨርሲቲው ገንዘቡ | |

| | | |
|---|---|---|
| | እንዲመለስ ለማድረግ እንደሚቸግረው በመግለፅ የሚመለከት የመንግስት አካል መመሪያ እንዲሰጥበት ያቀረበው ጥያቄ ምላሽ አለመሰጠቱ | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | በተሰጠ ኦዲት አስተያት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ በኦዲት ወቅት የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዳይታረሙ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ምንም እንኳን ዩኒቨርሲቲው ካሳውን የከፈለበት መነሻ ግንዛቤ አለመወሰዱ እና መፍትሄ ከሚመለከተው አካል ባይገኝም የዩኒቨርሲቲው አመራር ከህዳር ወር 2011 ዓም ጀምሮ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በየወሩ በድምሩ ብር 80,000 ወደ መንግስት ሂሳብ እንዲገባ ተደርጎ ተግባራዊ እየሆነ ነው፡፡ | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |

**በ2010 ዓም የፌዴራል ኦዲት የመጨረሻው ሪፖርት ላይ ስለቀረቡ ግኝቶች ዝርዝር ማብራሪያ**

**..... የቀጠለ**

| የጉዳዩ መለያ | የጉዳዩ መለያ ውጤት | ምርመራ |
|---|---|---|
| **ግኝት 14.1 እና 14.2 - የህጋዊነት/የክትትል ኦዲት /2003-2009/** | ለሱፐርቪዥን ወደተለያዩ ቦታዎች መምህራን ሲሄዱ በብልጫ የተከፈለ ብር 234, 214 እና በአንድ ሜጋ ፕሮጀክት ለተሳተፉ መምህራን የውሎ አበል ብር 120362.00 በአንድ ቀን ሁለት ግዜ በድምሩ ብር 354,576 አላግባብ መከፈሉ | |
| **መስፈርት** | ደንብና መመሪያ | |
| **መንስሄ** | በኮሌጆቹ በወቅቱ ከፍተኛ የፋይናንስ ባለሙያ እጥረት በመኖሩና ሰራተኞች በመልቀቃቸው እንዲሁም ተመራማሪው የቅፅ አሞላሉን አለማወቃቸው | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ሊባክን ይችላል | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | በወቅቱ ከሁለቱም ኮሌጆች ዲኖች ጋር በመነጋገር ማረጋገጥ የተቻለው ከላይ በመንስኤነት በተገለፀው ክፍተት ምክንያት የቅጽ አሞላል ስህተት እንጂ ሁን ተብሎ መምህራኑን ለመጥቀም የተሰራ ስራ አይደለም፡፡ ለዚህም ተመላሽ የሚደረግ ገንዘብ አይኖርም፡፡ ነገር ግን ክፍተቱ ትምህርት ተወስዶበት የቅጽ አሞላል በተተገቢው ትኩረት እንዲከናወን በማድረግ እንዲታረም ተደርጓል፡፡ | ከግኝት እንዲወጣ በመርሃ ግብሩ ዶኩመንት ላይ ተጠይቋል |
| **ግኝት 15 - የህጋዊነት/የክትትል ኦዲት /2003-2009/** | የግንባታ ሥራ ያቋረጡ ሥራ ተቋራጮች የጉዳት ካሳና የማቴሪያል ዋጋ በጠቅላላው ብር 63,077,064.58 ለዩኒቨርሲቲው ያልከፈሉ መሆኑ፤ | |
| **መስፈርት** | **ደንብና መመሪያ** | |
| **መንስሄ** | ተቋራጮች የግንባታ ስራውን ማቋረጣቸው | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | ግንባታው በወቅቱ አለመጠናቀቁ የዩኒቨርሲቲውን አገልግሎት ጥራት ያጓድላል፡፡ በአቋረጡት ላይ ተፈላጊ የመንግስት ሃብት እንዲመለስ አለመደረጉ በመንግስት ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ተጠያቂነትም ያመጣል | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | አንዱ ተቋራጭ ላይ ክስ ተመስርቶ የነበረ ቢሆንም በግልግል ዳኝነት እንዲታይ ተብሎ በፍርድ ቤት ሂደት ዘግይቶ አሁን ለዩኒቨርሲቲው በመወሰኑ ክሱ ቀጥሏል፡፡ ከአንዱ ጋር ጉዳዩ በድርድር እንዲታይ ተወስኖ በሂደት ላይ ነው፡፡ በሶስተኛው ላይ ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |
| **ግኝት 16 - የህጋዊነት/የክትትል ኦዲት ልዩ ልዩ** | የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት በመንግስት በተፈቀደለት የውስጥ መዋቅር መሰረት የሰው ሃይል ያልተሟላለት መሆኑ | |
| **መስፈርት** | መዋቅርና አደረጃጀት | |

| | | |
|---|---|---|
| **መንስዔ** | በገበያ ላይ ባለሙያ የመሳብ ችግርና የባለሙያዎች ፍልሰት | |
| **የሚያስከትለው ጉዳት** | የውስጥ ኦዲቱ  በበቂ የሰው ሃይል ካልተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓቱ ደካማ ሊሆን ይችላል | |
| **በዩኒቨርሲቲው የተወሰደ እርምጃ** | ዩኒቨርሲቲው ከውስጥም ከውጭም ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም የሰራተኛው ፍልሰት አስቸግሯል፡፡ አሁን ለዩኒቨርሲቲው በተፈቀደው በአዲሱ የስራ ምዘናና ግሬዲንግ መዋቅር መሰረት የሰው ሃይሉ እንዲሟላ ጥረት እየተደረገ ነው | በእርምት እርምጃ መርሃ ግብሩ ላይ ተመልክቷል |